በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የኅብረት ስራ ኮሚሽን
ANRS COOPERATIVE COMMISSION

ቁጥር ኅ/ስ/ኮ/10/08/18

ቀን 30/10/2018

ለሁሉም ዞን/ከተማ አስተዳደር ኅ/ስራ ማህበራት ማስ/ጽ/ቤት

ለሁሉም የኅብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁ/ብድር ዩኒዬኖች

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡ **<u>የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅ/ስራ ማህበራት የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 142/2018 የላከን መሆኑን ስለማሳወቅ</u>**

የአብክመ ኅብረት ስራ ኮሚሽን "የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት አፈጻጸም መመሪያ" በማዘጋጀትና በኮሚሽኑ ማኔጅመንት በማጸደቅ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ሰኔ 30/2018 ዓ.ም እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በኮሚሽኑ ድህረ ገጽ ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ለመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራትና ለኅብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች በዞኑ/በከተማ አስተዳደሩ በኩል እንዲደርስ እንድታደርጉ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

እንግዳ እማረ ገ/ህይወት
ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለኅብረት ስራ ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር
- ለኅብረት ስራ ሬጉላቶሪ ዳይሬክቶሬት
- ለኅብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ ምርመራ ዳይሬክቶሬት
- ለፋይናንስ ኅ/ስራ ማህበራት ልማትና አመራር ዳይሬክቶሬት

<u>ባህር ዳር</u>

ቁጥር ፡- የህ/ም/ማጠ/ዳ/1399/18
ቀን፡- 30/10/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ኅብረት ስራ ኮሚሽን

ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት የኅብረት ስራ ኮሚሽን በቁጥር ኅ/ስ/ኮ/1156/90/18 በቀን 30/10/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ስራ ኮሚሽን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት አፈጻጸም መመሪያ በማዘጋጀት ህጋዊነቱ ተመርምሮ ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል፡፡

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 142/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲውል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 32 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ገረመዉ እሸቱ
የህ/ም/ማ/ማ/ ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትሕ ቢሮ

Tel.No 058 222 0794/793 ✉ 995 Fax- 0582221530
☎ 058 220 37 57

መመሪያ ቁጥር 142/2018

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ሥራ ኮሚሽን የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት አፈጻጸም መመሪያ

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት ሰርተው ከሚያገኙት ገቢ ቀንሰው የቁጠባ ባህላቸውን በማሳደግ የፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ለማጎልበትና የኑሮ ደረጃቸውን ለማሻሻልና ማሕበራት ለአባላት የሚሰጡት የቁጠባና ብድር አገልግሎት የተሟላ፣ ምቹ፣ ቀልጣፋና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆን በየጊዜው አሰራሮችን ማሻሻል፣ አዳዲስና ጠቃሚ የሆኑ አገልግሎቶችን በማካተት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት የቁጠባና ብድር አገልግሎታቸውን አስተማማኝ ለማድረግና ከአባላት ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ለማጠናከር አነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ወሳኝ እንደሆነ በመታመኑ፤

ይህ አገልግሎት አባላት ገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ እና የተሻለ ካፒታል ለማፍራት በድንገት በሚከሰት ሞት ምክንያት በቤተሰብ አባላት ላይ የሚደርስን የገቢ መቋረጥ በተወሰነ ደረጃ ለማካካስ፣ የብድር መመለሻ የውል ስምምነት ጊዜው ሳይደርስና ብድራቸውን ከፍለው ሳያጠናቅቁ ከዚህ ዓለም በሞት የመለየት አደጋ በሚያጋጥማቸው ጊዜ ቀሪ ብድሩና ወለዱ የሚተካበትን ሁኔታ በማመቻቸት የተበዳሪ ቤተሰቦች ብድሩን ለመመለስ የሚደርስባቸውን ጫና ለማቃለልና የተበዳሪ ቤተሰቦችም በቀጣይ በተረጋጋ ሁኔታ ኑሯቸውን እንዲመሩ ለማስቻል ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ፤

በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት አነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት በብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ላይ በሙከራ ደረጃ አገልግሎቱ ካስገኘው ጠቀሜታ እና አገልግሎቶችን እየሰጡ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች ተሞክሮ በመውሰድ አገልግሎቱ ለክልላችን የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት አስፈላጊ

በመሆኑና አገልግሎቱ የሚመራበትን ሕጋዊ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የተጀመረውን የኅብረት ሥራ ሪፎርም በማፋጠን በአባላት ኑሮ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት ሊያግዝ የሚችል መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በክልሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 220/2007 አንቀጽ 66/2 እና በፌደራል የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 76(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአማራ ክልል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት አነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 142/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "አነስተኛ መድህን" ማለት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች በተመጣጣኝ ዋጋ የኢንሹራንስ ምርቶችን በማቅረብ አደጋዎችን እንዲቆጣጠሩ እና ከገንዘብ ኪሳራ እንዲያገግሙ የሚያደርግ አገልግሎት ነው፤

2/ "የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት /Credit Life Insurance/ ማለት አንድ አባል ከማኅበሩ ብድር ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በውል ስምምነቱ መሠረት ብድሩ እስኪመለስ ባለው ጊዜ ውስጥ ተበዳሪው ወይም የተበዳሪው ሚስት/ባል ብድሩን ከፍሎ ሳያጠናቅቅ ከዚህ ዓለም በሞት የመለየት አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ ቀሪ ብድሩ ከነወለዱ የሚሸፈንበት ወይም የሚካካስበት አሰራር ነው።

3/ "ወኪል" ማለት የብድር የህይወት መድህን ሰጭው የኅብረት ሥራ ማኅበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬን ወይም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር ሆኖ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎቱን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ወጭ ቆጣቢና ተደራሽ ለማድረግ በመሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ውስጥ ወይም በመሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሥራ ክልል በአባላት ከተቋቋመ የቁጠባ ቡድን ከሚገኙ የብድር የህይወት መድህን ተቀባዮች /Insured/ የአረቦን ክፍያ በመሰብሰብ የካሳ ጥያቄዎች ሲቀርቡ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከፍልና ለሰጠው አገልግሎት ከመድህን ዋስትና ሰጭው ኮሚሽን የሚከፈለው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው፡፡

4/ "አረቦን ወይም የብድር መድህን ዋስትና አገልግሎት ቅድመ-ክፍያ" ማለት የብድር የህይወት መድህን ተቀባዩ አገልግሎቱን ለማግኘት ለመድህን ሰጭው የሚከፍለው ገንዘብ ነው፡፡

5/ "ሞት" ማለት አንድ ሰው ሕይወቱ ማለፉ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ ነው፡፡ ሆኖም የአንድ ሰው መጥፋት ወይም አለመታየት እንደ ሞት ሊቆጠር የሚችለው በፍርድ ቤት የመሞት ግምት ውሳኔ ሲሰጥበት ብቻ ነው፤

6/ "ኮሚሽን" ማለት ለህብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒየኖች በውክልና አረቦን የመሰብሰብና ካሳ የመክፈል ስራ የሚሰራ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር ለአገልግሎቱ የሚከፈለው ክፍያ ነው፡፡

7/ "ተካፋል ተአውኒ" ማለት መተባበርን እና መረዳዳትን መሰረት በማድረግ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በሚሰጡ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት የሚሰጥ አነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ነው፡፡

8/ "የትዳር ጓደኛ" ማለት ብድሩ በሚሰጥበት ወቅት ተበዳሪ ሆኖ ከሚፈርመው ግለሰብ ጋር በትዳር አብሮ እየኖረ በአነስተኛ የብድር መድህን አገልግሎት ውል ላይ የትዳር ጓደኛ በሚለው የሚፈርም ሰው ነው፡፡

9/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

10/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው በሙሉ የሴትን ጾታ ያካትታል፡፡

3. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 220/2007 እና በፌዴራል ኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሠረት በተደራጁ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች እና የብድር ተጠቃሚ አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. የመመሪያው ዓላማ

1/ አባላት በሞት ምክንያት ቢለዩ የጀመሯቸው የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ሳይቋረጡ በወራሾቻቸው እንዲቀጥሉ በማድረግ፣ በቤተሰብ ላይ የሚደርሰውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና መቀነስ፤

2/ አባላት "ለቤተሰብ ዕዳ አላወርስም" በሚል ስጋት ከብድር አገልግሎት እንዳይገለሉ በማበረታታት፣ ብድራቸውን ሳይጨርሱ ቢሞቱ በቤተሰብ ላይ የሚፈጠረውን የክፍያ ጫና በማቃለል ኑሯቸውን በተረጋጋ ሁኔታ እንዲመሩ ማስቻል፤

3/ የማኅበሩን የብድር አመላለስ ጥራትና የፋይናንስ ደህንነት በዘላቂነት ማረጋገጥ፤ ናቸው፡፡

5. መሠረታዊ የመድህን አገልግሎት መርሆዎች

የመድህን ወይም ኢንሹራንስ አገልግሎት የሚመራባቸዉ መሰረታዊ መርሆዎች፣

1/. ጉዳትን ወይም ኪሳራን/ መሸፈን/ (Indemnity)፦ የመድህን ወይም ኢንሹራንስ አገልግሎት የሚሰጠው ጥቅም የመድህን ወይም ኢንሹራንስ ተጠቃሚው በገባው የመድህን ወይም ኢንሹራንስ ዓይነትና መጠን ልክ የሚደርስ ጉዳት/ኪሳራን ከመሸፈን ባሻገር ትርፍ አያስገኝም፤

2/ ጉዳትን ወይም ኪሳራን በገንዘብ መሸፈን (Insurable Interest)፦ የመድህን ወይም ኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚው በገባው የመድህን ኢንሹራንስ ዓይነትና መጠን ጉዳት ወይም ኪሳራ ሲደርስበት ጉዳቱ ወይም ኪሳራው የሚሸፈነው በገንዘብ ብቻ ነው፡፡

3/ መብትንና መወሰድ የሚገባውን መፍትሄ ማስተላለፍ (Subrogation)፦ መብትንና መወሰድ የሚገባውን መፍትሄ ከመድህን ወይም ኢንሹራንስ ተቀባዩ ወደ መድህን ወይም ኢንሹራንስ ሰጭው የማስተላለፍ መርህ ሲሆን መድህን ወይም ኢንሹራንስ ተቀባዩ መድህን ወይም ኢንሹራንስ የገባው ለአጠቃላይ ኢንሹራንስ ከሆነና መድህን ወይም ኢንሹራንስ ሰጭው በኢንሹራንስ ተቀባዩ ንብረት ላይ ጉዳት ከደረሰ የንብረቱን የባለቤትነት መብት በመረከብ ንብረቱን የማስጠገን እና ጉዳት ለደረሰበት የመድህን ወይም የኢንሹራንስ ተቀባይ አዲስ ተመሳሳይ ንብረት ገዝቶ መተካትን ያመለክታል፡፡ ይህ መርህ ለሕይወት መድህን ኢንሹራንስ አያገለግልም፡፡

4/ **እውነታን ማሳወቅ**/ (Utmost Good Faith)፦ መድህን ወይም ኢንሹራንስ ተቀባዩ ለሚገባው የኢንሹራንስ ዓይነትና ላጋጠመው አደጋ እውነተኛና ትክክለኛ መረጃ ለመድህን ኢንሹራንስ ሰጭው በግልጽ የማሳወቅ ግዴታን ይመለከታል፡፡

5/ **ጉዳትን ወይም ኪሳራን በመዋጮ ወይም በመጋራት መሸፈን**/ Contribution/ ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ የመድህን ወይም ኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በጋራ በወሰኑት ህግ መሰረት በአንድ የመድህን ወይም ኢንሹራንስ ሰጭ መድህን ወይም ኢንሹራንስ ተቀባይ/ አባል ላይ ጉዳት ወይም ኪሳራ ሲደርስ ጉዳቱን ወይም ኪሳራውን የመድህን ወይም ኢንሹራንስ ሰጭ ተቋማት በጋራ ወይም በመዋጮ የሚሸፍኑበት አሰራር ሲሆን ይህ መርህ ለሕይወት መድህን ኢንሹራንስ አያገለግልም፡፡

6/ **ለጉዳቱ ወይም ኪሳራው ቅርብና ቀጥተኛ የሆነውን ምክንያት በትክክል ማሳወቅ**/ (Causa Proxima)፦ የመድህን ወይም ኢንሹራንስ ሰጭው የመድህን ወይም ኢንሹራንስ ተቀባዩን ጉዳት ወይም ኪሳራ የመሸፈን ግዴታው ለጉዳቱ ወይም ኪሳራው ቅርብና ቀጥተኛ በሆነ ምክንያት ለሚፈጠር ጉዳት ወይም ኪሳራ ብቻ ነው፡፡ ለጉዳቱ ወይም ኪሳራው ቅርብና ቀጥተኛ ባልሆነ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት ወይም ኪሳራ በመድህን ወይም ኢንሹራንስ ሰጭው አይሸፈንም፡፡

ክፍል ሁለት

በአነስተኛ የብድር ህይወት መድን አገልግሎት ስለሚታቀፉ ተጠቃሚ አባላት፣ መብትና ግዴታ

6. በአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ስለ ሚታቀፉ አባላት እና የአገልግሎት ተጠቃሚነት

1/ በብድር የህይወት መድህን ወይም ኢንሹራንስ የሚታቀፉ አባላት የአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት በመሠረታዊ ኀብረት ስራ ማህበራት የሚሰጥ ከሆነ እስከ ብር 600,000 (ስድስት መቶ ሺ ብር) እና እስከ አስር ዓመት የብድር የቆይታ ጊዜ እንዲሁም የአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት በዩኒዬን የሚሰጥ ከሆነ እስከ ብር 800,000.00 /ስምንት መቶ ሺህ/ ብር እና እስከ አስር ዓመት የብድር የቆይታ ጊዜ ብድር የሚወስዱ አባላት ብቻ ናቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኀብረት ሥራ ማህበሩ የአነስተኛ የብድር መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን በጠቅላላ ጉባኤ መወሰን አለበት፤ በጠቅላላ ጉባኤ በአብላጫ ድምጽ ከተወሰነ ተበዳሪ አባላት የሚወስዱት ብድር ከብር 800,000.00 (ስምንት መቶ ሺ ብር) እስካልበለጠ ድረስ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፤

3/ ባለትዳሮች በአንድ ወይም በሁለት የተለያዩ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማኅበራት ተደራጅተው የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆኑ ባል ወይም ሚስት በሞት ቢለዩ የሟቹ ቀሪ ዕዳ እና ወለድ ብቻ ይሸፈናል፡፡

4/ ከባለትዳሮች አንደኛው ብቻ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ቢሆን ባል ወይም ሚስት በሞት ከተለዩ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚው ብቻ ቀሪ ዕዳና ወለድ ይሸፈናል፡፡

5/ ትዳር የሌለው/ላት እማወራ ወይም አባወራ የብድር ሕይወት መድን ከገባ/ች በኋላ በአዲስ ለሚያገባው/ውላት የትዳር አጋር የመድን ሽፋን አይሰጥም፡፡ ከአንድ በላይ ሚስት

ያላቸው ግለሰቦች ካሉ፣ ብድር በሚወስዱበት ጊዜ በውሉ ላይ የፈረመችው ሚስት ብቻ የብድር ሕይወት መድን ሽፋን ተጠቃሚ ትሆናለች።

6/ ባለትዳሮች የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ውል ከገቡ በኋላ ፍቺ ቢፈጸምና ተበዳሪው በሞት ቢለይ የተፈታው ባል ወይም ሚስት አገልግሎቱን የማያገኝ ሲሆን የተበዳሪው ሕጋዊ ወራሽ/ሶች ብቻ የካሳ ክፍያው ተጠቃሚ ይሆናሉ።

7. የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብቶችና ግዴታዎች

1/ ማንኛውም የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን ተጠቃሚ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል።

ሀ) በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው የብድር ህይወት መድህን ዋስትና መጠንና የብድር ቆይታ ጊዜ መሰረት ማኅበሩ የሚሰጠውን የብድር የህይወት መድህን ዋስትና አገልግሎት የማግኘት፣

ለ) አባሉ ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ በዚህ መመሪያ መሰረት በወራሽ/ሾች በሚቀርብ ጥያቄና ማስረጃ የአሟሟቱ ሁኔታ ተጣርቶ እና አስፈላጊው ህጋዊ ማስረጃ መሟላቱ ከተረጋገጠ በኋላ በውሉ መሰረት እጅግ ቢበዛ በ 3 (ሶስት) የስራ ቀናት ውስጥ የተበዳሪው ቀሪ ዕዳ እና ወለድ ቀሪ የመሆን፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ለ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሞት አደጋ ስለመከሰቱ ሕጋዊ ማስረጃዎች ከቀረቡ በኋላ የቀብር ማስፈጸሚያ የማግኘት፤

2/ ማንኛውም የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን ተጠቃሚ አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል።

ሀ) በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነውን የአረቦን መጠን መሰረት በማድረግ የተፈቀደለትን ብድር ከመውሰዱ በፊት አረቦን በቅድሚያ የመክፈል፣

ለ) የተበደረውን ብድር በብድር ማመልከቻው መሰረት ለተፈቀደለት ተግባር ብቻ የማዋል፣

ሐ) ተበዳሪው በህይወት እያለ የተበደረውን ብድር ወቅቱን ጠብቆ የመክፈል፣

መ) የሞት አደጋ ሲያጋጥም በሕጋዊ ወራሽ/ሾች የተፈረመ ማመልከቻና የሞት ማስረጃ ከሚመለከተው ሕጋዊ አካል ማቅረብ፣

ሠ) የካሳ ክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ የጋብቻ የምስክር ወረቀት (ሰርተፍኬት ከሲቪልና ቤተሰብ አገልግሎት ወይም ወሳኝ ኩነት ወይም ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎችን አግባብ ካለው አካል የማቅረብ፣

3/ የወኪል የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ሰጪ የተበዳሪዎች ባል/ሚስት የሞት አደጋ ሲያጋጥም የካሳ ክፍያውን ከአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ሰጪው ወይም ከዩኒዬኑ ወጪ አድርገው ከመክፈላቸው በፊት የሚከተሉትን ግዴታዎች ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ)የብድር የህይዎት መድህን አገልግሎት ውል በማህበሩ ሰብሳቢ የጸደቀና የማኅበሩ ክብ ማህተም ያለበት፤

ለ) ተበዳሪ አባላት ለማህበሩ አርቦን ገቢ ያደረገበት ደረሰኝ ኮፒ ማቅረብ፤

ሐ) ማህበሩ ከአባላት ሰብስቦ ለዩኒየኑ የአርቦን ክፍያ ገቢ ያደረገበት ደረሰኝ ኮፒ፤

መ) የጋብቻ የምስክር ወረቀት (ሰርተፍኬት ከሲቪልና ቤተሰብ አገልግሎት ወይም ወሳኝ ኩነት ወይም ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎችን አግባብ ካለው አካል የማቅረብ፣

ሠ) የተበዳሪ አባል የባልና የሚስት መታወቂያ፤

ረ) የዉክልና ውል እና

ሰ) የተበዳሪዉ የብድር ውል እና ብድር የወሰደበት የወጭ ደረሰኝ ሁለተኛው ጥራዝ፤

ክፍል ሦስት

የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት የአረቦን አወሳሰን፣ የአረቦን አከፋፈል፣ የአገልግሎት ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሁኔታዎችና ከአገልግሎቱ የሚገኝ ጥቅም

8. የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ቅድመ ክፍያ ወይም አረቦን ስለሚከፈልበት ሁኔታ

የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ቅድመ ክፍያ ወይም አረቦን መጠን የሚከፈለው፡-

1/ ሊኖር የሚችለውን የሞት አደጋ ግምት፣ የስራ ማስኬጃ ወጪዎችና ተመጣጣኝ ትርፍ ታሳቢ በማድረግ፤

2/ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የህብረት ስራ ማህበራት የአረቦን መጠን ፍትሃዊ ለማድረግ እያንዳንዱ ተበዳሪ አባል ወይም የቡድን አባላት የሚወስደውን የብድር መጠን፣ ብድሩ የሚመለስበትን ጊዜ እና የጋብቻ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

9. የብድር ህይወት መድህን አረቦን አወሳሰንን በተመለከተ፣

በአንድ ጊዜ የሚከፈለው አረቦን መጠን የሚወሰነው፣

1/ በአመላለስ ሁኔታው፣

2/ የብድር የቆይታ ጊዜ፣

3/ በብድር መጠኑ እና

4/ ትዳር ያለውና የሌለው የሚለውን መነሻ በማድረግ ይሆናል፤

5/ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚከፍሉት የአረቦን መጠን ዝቅተኛው 1.25 ፐርሰንት ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 2.1 ፐርሰንት ይሆናል፤ ዝርዝሩ በአባሪ አንድ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡

10.የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

1/ የብድር የህይወት መድህን ዋስትና አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑት ተበዳሪ አባላት በገቡት የብድር መመለሻ ጊዜ ውል ስምምነት ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የማኅበሩ የብድር መድህን ዋስትና ውል እድሜ ብድሩ ተጠናቆ የሚከፈልበት ጊዜ ብቻ ይሆናል፤

2/ ተበዳሪው አባል ሌላ ብድር ሲወስድ በአዲስ ለሚወስደው ብድር እንደገና አረቦን መክፈል ይኖርበታል፤ የብድር መድህን ዋስትና ውልም በአዲስ ይያዛል፤ የአረቦን መጠኑም እንደሚወስደው የገንዘብ መጠንና የአከፋፈል ሥርዓት መሠረት ያደረገ ይሆናል፤

3/ የብድር የህይወት መድህን ዋስትና አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ተበዳሪ የተሰማራበት የሥራ መስክ ተጨማሪ ብድር የሚያስፈልገው ሆኖ ከተገኘና በማህበሩ የብድር መመሪያ መሠረት ተጨማሪ ብድር ከተፈቀደለት በአዲስ ለወሰደው ተጨማሪ ብድር በአዲስ ውል በመያዝ አረቦን ሊከፍል ይገባል፤

4/ አንድ ተበዳሪ በማህበሩ የብድር መመሪያ መሰረት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የብድር መመለሻ ጊዜ እንዲራዘምለት ጠይቆ በማህበሩ ታምኖበት ፍቃድ ካገኘ የቀሪ ብድር መጠንና የብድር አከፋፈሉን መሰረት በማድረግና በአዲስ ውል በመውሰድ እንደገና አረቦን መክፈል ይኖርበታል፤

5/ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎቱን መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚሰጡ ከሆነ ተበዳሪው የብድር መመለሻ ጊዜው ሳይደርስ አስቀድሞ ብድሩን የሚከፍል ከሆነ ብድሩን አጠናቆ ከከፈለበት ጊዜ ጀምሮ የአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ውሉ ይቋረጣል፤

6/ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር በኤጀንትነት የአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት የሚሰጥ እና ዩኒዬኑ የአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ሰጪ ከሆነ እና ተበዳሪ ግለሰቦች ብድሩን ለመሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበሩ ሳይመልሱ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር መመለሻ ጊዜው ሳይደርስ ለዩኒዬኑ ቢመልስ በመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበርና ዩኒዬን መካከል ያለው ውል የሚቋረጥ ስለሆነ ተበዳሪው የብድር

መመለሻ ጊዜው ሳይደርስና ብድሩን ከፍሎ ሳይጨርስ በሞት ቢለይ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበሩ የተበዳሪውን ቀሪ ዕዳና ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት፤

7/ በአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ተበዳሪ በህይወት እያለ የመመለሻ ጊዜውን ጠብቆ ሳይከፍል ለቆየው እና ለፈጠረው ውዝፍ ብድር የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን ሽፋን የማያገኝ ሲሆን ከሞተበት ቀን ጀምሮ ያለው ቀሪ ብድር እና ወለድ ብቻ ይሸፈንለታል።

11. ከአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት የሚገኝ ጥቅም

1/ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ተበዳሪ ወይም የትዳር አጋር በሞት በሚለይበት ወቅት የሞት ማረጋገጫ ማስረጃ እንደቀረበ ያለበት ብድር ዋናና ወለድ ይሸፈንለታል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ወራሾች የሚቹን ሕጋዊ ማስረጃ ማቅረባቸውና ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸሚያ ብር 2000.00 (ሁለት ሺህ ብር) ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል፤

3/ ተበዳሪው የሚከፍለው የአረቦን መጠን የፀደቀለትን የብድር መጠን ብቻ መሠረት ያደረገና ወለድን ሳይጨምር ቢሆንም በመድህን ዋስትና የሚሸፈነው ግን ከተበዳሪው የሚጠበቅ ዋናና ወለድ እንዲሁም የቀብር ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸሚያ ወጪ ጨምሮ ነው።

12. የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ሰጪ (የኅብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬን) እና ወኪል (የመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት) ተግባርና ኃላፊነት

1/ የህብረት ሥራ ማኅበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒየኖች ለሚሰጡት አነስተኛ የብድር የህይወት የመድህን አገልግሎት ከመሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማሕበራት ውጪ ሌላ ወኪል መጠቀም አይችሉም፤

2/ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማሕበራት ለኅብረት ሥራ ማኅበራት የቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች ወኪል ሆነው አገልግሎቱን ይሰጣሉ፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማሕበሩ የአባላት ቁጥር 1,500 (አንድ ሺ አምስት መቶ) እና በላይ እንደዚሁም የወረተ ዕጣና መደበኛ ቁጠባ ጠቅላላ ድምር 35,000,000 (ሰላሳ አምስት ሚሊዬን) እና በላይ ከሆነ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ በራሳቸው የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎቱን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

4/ ወኪል መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማሕበራት በውክልና የሰበሰቡትን አረቦን እና የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች መረጃ በታማኝነት የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፤

5/ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት የኮሚሽን ክፍያን በተመለከተ የኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬን ከተሰበሰበው አረቦን ውስጥ 15 በመቶ ለውክልና አገልግሎት ሰጪው መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር ይከፍላል፡፡

6/ ወኪል መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከተበዳሪዎች የሰበሰቡትን አረቦን 15 በመቶ ኮሚሽን በመቀነስ ቀሪውን የተሰበሰበ አረቦን በየዕለቱ ለኅብረት ሥራ ማሕበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒየን ገቢ ማድረግ አለባቸው፤ ነገር ግን ባንክ በአቅራቢያ ባለመኖሩ ከ2 ሰዓት በላይ የእግር ጉዞ በሚያስኬዱ አካባቢዎች እጅግ ቢዘገይ እስከ ሦስት ቀናት ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማሕበሩ በ3 ቀናት ውስጥ ከተበዳሪዎች የተሰበሰበውን አረቦን ካላስገባ እና በእነዚህ ቀናት ውስጥ የተበዳሪዎች ወይም የተበዳሪዎች ባል/ሚስት የሞት አደጋ ቢከሰት የካሳ ክፍያውን መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማሕበሩ ይከፍላል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባንክ በአቅራቢያ ባለመኖሩ ከ2 ሰዓት በላይ የእግር ጉዞ በሚያስኬዱ አካባቢዎች በሦስት ቀናት የተሰበሰበው አረቦን ለዩኒዬኑ ገቢ ሳይደረግ የተበዳሪው ባል/ሚስት ላይ የሞት አደጋ ከተከሰተ ዩኒዬኑ የተሰበሰበውን አረቦን ተቀብሎ የካሳ ክፍያውን ይፈጽማል፤

9/ የሞት አደጋ ሲያጋጥም መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማሕበራት ማስረጃው ከተጣራ በኋላ ለሟች ወራሾች በሦስት ቀናት ውስጥ ከዩኒየኑ በሕጋዊ ደረሰኝ ወጪ በማድረግ ክፍያ ይፈጽማሉ፤

10/ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎቱን በተመለከተ ወኪሎችና አገልግሎት ሰጪዎች ሪፖርትና መረጃ የመስዋወጥና ተጠሪ ለሆኑባቸው የአደራጅ ተቋሙ አካላት የመግለጽ ግዴታ አለባቸው፡፡

ክፍል አራት

የወለድ አልባ የአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት

13. የተካፉል ተአውኒ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

1/ የተካፉል ተአውኒ አነስተኛ የብድር የህይወት የመድን ዋስትና አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ማንኛውም አባል የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፤

ሀ) የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን፣

ለ) የተወሰነውን አረቦን መክፈል፣

2/ የአረቦን መጠን የሚወሰነው ለሚደርሰው ጉዳት የሚከፍለውን ገንዘብ እና የአስተዳደራዊ ወጪን መሸፈን እንዲችል ተደርጎ መሆን አለበት፤

3/ በቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማህበሩ የተሰበሰበውን አረቦን የአባልን ጉዳት ለመካስ ወይም ኪሳራን ለመሸፈን መሆን አለበት፤

4/ በወለድ አልባ የአነስተኛ የብድር የሕይወት መድህን አገልግሎት የካሳ ክፍያ የሚፈጸመው ተበዳሪው በሞት ከተለየ በኋላ ያለው ቀሪ ዕዳ እና በውል የተያዘው የትርፍ ህዳግና ወጪ ወይም ኮሚሽን የሚሸፈን ይሆናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ከተጠቀሱት በተጨማሪ በዚህ መመሪያ የተደነገጉ መብቶችና ግዴታዎች ለወለድ አልባ የአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል አምስት

ጉዳት ሲደርስ መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች፣ በአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን የማይሸፈኑ ጉዳዮች፣ የአጋር አካላት ግዴታና የሪፖርት ሥርዓት

14. ጉዳት ሲደርስ መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች

የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት የሚያስገኘውን ጥቅም ማግኘት የሚቻለው ተበዳሪው ስለመሞቱ ከሚመለከታቸው አካላት የሚከተሉት ሕጋዊ ማረጋገጫዎች ወይም ማስረጃዎች ሲያቀርቡ ብቻ ነው፡፡

1/ ተበዳሪው ስለመሞቱ ወራሾች ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው፣

2/ ተበዳሪው ስለመሞቱ የሚያረጋግጥ የሞት ማረጋገጫ ህጋዊ ከሆነ አካል በህጋዊ ማህተም የተደገፈ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ለተጠቀሰው የሚቀርብ ማስረጃ ከሲቪልና ቤተሰብ አገልግሎት ወይም ከወሳኝ ኩነቶች፣ ከቀበሌ አስተዳደር ወይም ከሆስፒታል/ የጤና ተቋም ወይም ከፖሊስ ወይም ከሃይማኖት ተቋማት ወይም ከዕድር መሆን አለበት፤

4/ የሚቀርበው የሞት ማስረጃና ማመልከቻ ይዘት ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት በተያያዙት ቅፆች መሰረት መሆን ይኖርበታል፤

5/ የመድህን ወይም ኢንሹራንስ ሽፋኑ ተጠቃሚ ለመሆን ወራሾች የሚያቀርቡት ማመልከቻ እና ከማንኛውም ህጋዊ አካል የሚቀርብ የሞት ማረጋገጫ ማስረጃ ተበዳሪው እንደሞተ ቢበዛ እስከ ሁለት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ለመሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኀብረት ሥራ ማኅበሩ መቅረብ አለበት፤ ከሁለት ወር በላይ ዘግይቶ የሚቀርብ ማረጋገጫ አሳማኝ ምክንያት ካለው ብቻ እስከ አንድ ወር ሊራዘም ይችላል፤

6/ ከሦስት ወር በላይ ዘግይቶ የሚቀርብ የሞት ማስረጃ በምንም መልኩ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አይቻልም፤ ሆኖም፣ በአሳማኝ ምክንያት ከ 3 ወር በኋላ የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ውሳኔ ይሰጥበታል።

7/ ከላይ የተጠቀሱት ማስረጃዎች ተሟልተው እንደቀረቡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን ሽፋኑ ተግባራዊ ይሆናል፤

8/ የቀረቡትን ማስረጃዎች ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣ ክፍያ የማፅደቅና የመፈጸም ኃላፊነትና ሥልጣን ሙሉ በሙሉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበራት የቁጠባና ብድር ዩኒዬኑ ይሆናል።

9/ የሞት ማስረጃው ህጋዊነት ሳይረጋገጥ በተሳሳተ ማስረጃ ክፍያ የፈጸመ ማስረጃው ስህተት መሆኑ ከተረጋገጠ የኅብረት ስራ ማህበሩ ሊቀመንበር ወይም ምክትል ሊቀመንበር ወይም ስራ አስኪያጅ በስህተት የተከፈለውን የካሳ ክፍያ ገንዘብ መጠን ተጠያቂ ይሆናል።

15. በአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት የማይሸፈኑ ጉዳዮች

1/ በውል ስምምነት የጊዜ ገደብ ውስጥ በተበዳሪው እና የትዳር አጋሩ/ሯ ላይ ከሚፈጠር የሞት አደጋ ውጭ በተበዳሪው/ዋ ላይ የሚፈጠሩ ማናቸውም ችግሮች በዚህ መድህን አገልግሎት አይሸፈኑም።

2/ አንድ ተበዳሪ አባል ሆን ብሎ ራሱን ያጠፋ ከሆነ ወይም በህገ-ወጥ ተግባር ተሰማርቶ ለማምለጥ በሚያደርገው ሙከራ ከሞተ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን ሽፋን ተጠቃሚ አይሆንም።

3/ መጥፋቱ ተረጋግጦ የመሞቱ ውሳኔ በፍርድ ቤት ካልተሰጠ በስተቀር አንድ ተበዳሪ አባል ከአካባቢው ቢሰወር የመድህን ሽፋን አያገኝም።

4/ አንድ ተበዳሪ አባል ከብድር መመለሻ ጊዜው በፊት አስቀድሞ ብድሩን ቢከፍል የኢንሹራንስ ዋስትናው ለብድሩ የተገባበት በመሆኑ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ውሉ ብድሩን በከፈለበት እለት ይቋረጣል፤ በመሆኑም ብድሩን

ከከፈለ በኂላ ለሚፈጠር የሞት አደጋ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ሽፋን አይኖርም፡፡

5/ ከመሞቱ በፊት ተበዳሪው ለፈጠረዉ ዉዝፍ ብድር መጠን የብድር ህይወት መድህን ሽፋን አያገኝም፡፡

6/ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ማለትም ድርቅ፣ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ሰደድ እሳት፣ ወረርሽኝ የሚከሰት የሞት አደጋ የብድር ህይወት መድህን ሽፋን አያገኝም፤

7/ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ማለትም ጦርነት እና የብሔር ወይም የጎሳ ግጭት የብድር ህይወት መድህን ሽፋን አያገኝም

16.የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የሞትና አሟሟት ማረጋገጫ የሚሰጡ ተቋማት ተበዳሪው ስለመሞቱ እና ስለአሟሟቱ ትክክለኛ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

2/ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡት ማስረጃ የሚመለከተው ባለስልጣን የፈረመበትና ህጋዊ ማህተም የተደረገበት ሊሆን ይገባል፡፡

3/ የሚቀርበው ማስረጃ ታማኝነት ያለውና ወቅታዊ መሆን አለበት፡፡

17. ሪፖርትና መረጃ

1/ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት የሚሰጠው መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር /ዩኒዬን ተጠሪ ለሆነበት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኮሚሽን አካል በየወሩ ከመደበኛ ሪፖርት ጋር መላክ ይኖርበታል፡፡

2/ የሚቀርበው ማስረጃ ጥራቱን የጠበቀና ታማኝ መረጃ ሊሆን ይገባል፡፡

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18.ስለ ተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

1/ በሙከራ ደረጃ በሥራ ላይ ያለው የቁጠባ መር እና የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት የአፈፃፀም ማኗል በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር ቢኖር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

19. ስለ ተጠያቂነት

1/ ኅብረት ስራ ማህበራትም ሆነ የክልሉ የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ያለው የኮሚሽኑ አካላት ይህን መመሪያ የማክበር ወይም የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ ከተደነገገው አሰራር ውጭ መመሪያውን በማዛባት ተፈጻሚ እንዲሆን ያደረገ በየደረጃው የሚገኝ የኮሚሽኑ ማንኛውም ኃላፊና ባለሙያ፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ አባል፣ ወይም ሥራ አስኪያጅ ወይም ቅጥር ሠራተኛ በኅብረት ሥራ ኮሚሽኑ የሥነ-ምግባር ደንብ ወይም አግባብነት ባለው የወንጀል ወይም የፍትሓብሔር ሕግ መሠረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፡፡

20.ስለ አባሪዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት የተያያዙ አባሪዎችና ቅጻ ቅጾች የመመሪያው አካል ሆነው በሚመለከታቸው አካላት እየተሞሉ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

21.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1/ ሰኔ 30 ቀን 2018 ዓ.ም በህብረት ስራ ኮሚሽን ጸድቋል፡፡

2/ ሰኔ 30 ቀን 2018 ዓ.ም በአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ ተመዝግቧል፡፡

3/.................. ቀን 2018 ዓ.ም በህብረት ስራ ኮሚሽን ድህረ ገጽ ተጭኗል፡፡

ባህርዳር

ጌትነት አማረ ገ/ህይወት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር

የህብረት ስራ ኮሚ...

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ... The ANRS Bureau of Justice

አባሪዎች እና ቅጻ ቅፃች

አባሪ አንድ

ለአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ለማግኘት የሚከፈል የአረቦን መጠን አወሳሰንን በተመለከተ

የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብድር ከመውሰዳቸው በፊት በአንድ የክፍያ ጊዜ ከዚህ በታች በተቀመጠው ፐርሰንት መሰረት የሚከፍሉ ይሆናል፡-

1/ የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚከፍሉት የአረቦን መጠን ዝቅተኛው 1.25 ፐርሰንት ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 2.1 ፐርሰንት ይሆናል፡፡

2/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩ የሚመለስ አንድ ዓመትና ከዚያ በታች የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.25%፣

3/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩ የሚመለስ አንድ ዓመትና ከዚያ በታች የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.30%፣

4/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ሆኖ በአንድ ጊዜ የሚመለስ አንድ ዓመትና ከዚያ በታች የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.30%፣

5/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ሆኖ በአንድ ጊዜ የሚመለስ አንድ ዓመትና ከዚያ በታች የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.35%፣

6/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.35%፣

7/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.40%፣

8/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100000 (አንድ መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በአንድ ጊዜ የሚመለስ እና ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለው አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.45%፣

9/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100000 (አንድ መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በአንድ ጊዜ የሚመለስ እና ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.50%፣

10/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.40%፣

11/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.45%፣

12/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100000 (አንድ መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በአንድ ጊዜ የሚመለስ እና ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለው አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.50%፣

13/ የብድር መጠኑ እስከ ብር 100000 (አንድ መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በአንድ ጊዜ የሚመለስ እና ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.55%፣

14/ የብድር መጠኑ ከ100000 በላይ እስከ ብር 300,000 (ሶስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.45%፣

15/ የብድር መጠኑ ከ100000 በላይ እስከ ብር 300,000 (ሶስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.50%፣

16/ የብድር መጠኑ ከ100000 በላይ እስከ ብር 300,000 (ሶስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.50%፣

17/ የብድር መጠኑ ከ100000 በላይ እስከ ብር 300,000 (ሶስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.55%፣

18/ የብድር መጠኑ ከ300000 (ሶስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.50%፣

19/ የብድር መጠኑ ከ300000 (ሶስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.55%፣

20/ የብድር መጠኑ ከ300000 (ሶስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.55%፣

21/ የብድር መጠኑ ከ300000 (ሶስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት

ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.60%፣

22/ የብድር መጠኑ ከ300000 (ሶስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ሰባት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.60%፣

23/ የብድር መጠኑ ከ300000 (ሶስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ሰባት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.65%፣

24/ የብድር መጠኑ ከ300000 (ሶስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሰባት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.65%፣

25/ የብድር መጠኑ ከ300000 (ሶስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሰባት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.70%፣

26/ የብድር መጠኑ ከ500,000 (አምስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.70%፣

27/ የብድር መጠኑ ከ500000 (አምስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.75%፣

28/ የብድር መጠኑ ከ500000 (አምስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.75%፣

29/ የብድር መጠኑ ከ500000 (አምስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.80%፣

30/ የብድር መጠኑ ከ500000 (አምስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ሰባት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.80%፣

31/ የብድር መጠኑ ከ500000 (አምስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ሰባት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.85%፣

32/ የብድር መጠኑ ከ500000 (አምስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሰባት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.85%፣

33/ የብድር መጠኑ ከ500000 (አምስት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሰባት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.90%፣

34/ የብድር መጠኑ ከ700,000 (ሰባት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአንድ

ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.90%፣

35/ የብድር መጠኑ ከ700,000 (ሰባት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩ የሚመለስ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ ሶስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.95%፣

36/ የብድር መጠኑ ከ700,000 (ሰባት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 1.95%፣

37/ የብድር መጠኑ ከ700,000 (ሰባት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሶስት ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 2.0%፣

38/ የብድር መጠኑ ከ700,000 (ሰባት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ሰባት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 2.0%፣

39/ የብድር መጠኑ ከ700,000 (ሰባት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ሰባት ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 2.05%፣

40/ የብድር መጠኑ ከ700,000 (ሰባት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በየወሩ፣ በየሶስት ወሩ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ የሚመለስ ከሰባት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር የሌለዉ አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 2.05%፣

41/ የብድር መጠኑ ከ700,000 (ሰባት መቶ ሺ.) በላይ እስከ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺ. ብር) ሆኖ በአንድ ጊዜ የሚመለስ እና ከሰባት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት የሚቆይ ብድር የሚወስድ ትዳር ያለው አባል የሚወስደውን የብድር መጠን 2.1%።

<u>አባሪ ሁለት</u>

<u>የሂሳብ አመዘጋገብና የመጠባበቂያ ተቀማጭ ሂሳብ</u>

1. <u>የሂሳብ አመዘጋገብ</u>

በአረቦን አሰባሰብ እና በሞት ለተጎዱት የካሳ ክፍያ ሲፈጸም አመዘጋገቡ በሚከተለው መንገድ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1/ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማሕበራት ወኪል ሆነው የኅብረት ሥራ ማሕበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዩን የአነስተኛ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ሰጪ በሚሆንበት ጊዜ በኅብረት ሥራ ማሕበር ደረጃ የሚከተሉት ምዝገባዎች ይከናወናሉ፡፡

ሀ) አረቦን ሲሰበሰብ

(1) ጥሬ ገንዘብ XXX

(2) ተከፋይ የብድር የህይዎት መድህን XXX

(3) *(ማጣቀሻ፡ የገንዘብ መሰብሰቢያ ሰንጠረዥ)*

ለ) የአገልግሎት ክፍያ (ኮሚሽን) አፈጻጸም

(1) ተከፋይ የብድር የህይዎት መድህን አረቦን (15%) ... XXX

(2) የብድር የህይዎት መድህን አገልግሎት ኮሚሽን ገቢ ... XXX

ሐ) አረቦን ወደ ዩኒየን ሲላክ

(1) ተከፋይ የብድር የህይዎት መድህን አረቦን (85%) ... XXX

(2) ጥሬ ገንዘብ XXX

መ) በካሳ ክፍያ ጊዜ

(1) የብድር የህይዎት መድህን አረቦን ተሰብሳቢ ከዩኒዬን ... XXX

(2) ጥሬ ገንዘብ XXX

(3) *ማጣቀሻ፡ የወራሾች የካሳ ክፍያ ማመልከቻና የሞት እና አሟሟት ማረጋገጫ)*

ሠ) መድህን ሰጪ ዩኒዬን ብሩን ሲልክ ለመሰረታዊ ወኪሎቻቸው ጋር የሚያደርጉት የሂሳብ እንቅስቃሴ

(1) ጥሬ ገንዘብ XXX

(2) የብድር የህይዎት መድህን የተሰበሰበ አረቦን XXX

2/ በመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር ደረጃ አገልግሎቱ የሚሰጥ ከሆነ የሚከተሉት ምዝገባዎች ይከናወናሉ፡፡

ሀ) አረቦን ሲሰበሰብ

(1) ጥሬ ገንዘብ XXX

(2) ተከፋይ የብድር የህይዎት መድህን XXX

(3) *(ማጣቀሻ፡ የገንዘብ መሰብሰቢያ ሰንጠረዥ)*

ለ) የሽፋን ጊዜው ተጠናቅቆ የብድር የህይዎት መድህን የመጠባበቂያ ጣሪያ እስኪሞላ ድረስ

(1) ተከፋይ የብድር የህይዎት መድህን XXX

(2) የብድር የህይዎት መድህን (አረቦን) መጠባበቂያ XXX

ሐ) የሽፋን ጊዜው ተጠናቅቆ የብድር የህይዎት መድህን ወደ ገቢነት ሲቀየር ከመጠባበቂያ በኋላ

(1) ተከፋይ የብድር የህይዎት መድህን XXX

(2) ከብድር የህይዎት መድህን አገልግሎት የተገኘ ገቢ XXX

የህብረት ስራ ...
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ... ማርቀቅና ... ዳይሬክቶሬት
The ANRS Bureau of Justice

3/ የአነስተኛ የብድር ህይወት መድህን አገልግሎት ሰጪ የኅብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒየኖች የሚኖር ምዝገባ፦

ሀ) ከወኪሎች አረቦን ሲቀበል

ጥሬ ገንዘብ XXX

ተከፋይ የብድር የህይወት መድህን ዋስትና XXX

ለ) በወኪል መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት በኩል ካሳ ሲከፍል

- ተከፋይ የብድር የህይወት መድህን XXX
  - ጥሬ ገንዘብ XXX

ሐ) የሽፋን ጊዜው ተጠናቅቆ የብድር የህይወት መድህን የመጠባበቂያ ጣሪያ እስኪሞላ ድረስ

- ተከፋይ የብድር የህይወት መድህን XXX
- ከብድር የህይወት መድህን (አረቦን) መጠባበቂያ XXX
- *(ማጣቀሻ፡ በሂሳብ ሰራተኛ የሚቀርቡ ሰነዶችና ማመልከቻ)*

መ) የሽፋን ጊዜው ተጠናቅቆ የብድር የህይወት መድህን ወደ ገቢነት ሲቀየር ከሪዘርቡ በኋላ

- ተከፋይ የብድር የህይወት መድህን XXX
- ከብድር የህይወት መድህን አገልግሎት የተገኘ ገቢ XXX

2. <u>የአረቦን መጠባበቂያ ተቀማጭ መጠን</u>

ሀ) በዚህ መመሪያ መሰረት ከተበዳሪዎች የሚሰበሰበው አረቦን ዓላማው በሞት የሚጎዱ ተበዳሪዎች ቤተሰብ ወደ አልተፈለገ ዕዳ ገብተው ጉዳት እንዳይደርስባቸው ቀሪ

ዕዳቸውን በመሸፈን መከላከል ሲሆን፤ የካሳ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ቀሪው ገንዘብ በአግባቡ መተዳደር አለበት።

ለ) የካሳ ክፍያው ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ የገንዘብ እጥረት እንዳይገጥም ከተሰበሰበው አረቦን የመጠባበቂያ መጠን እንደሚከተለው ይያዛል፦

1) አገልግሎት ሰጪው ዩኒዬን ከሆነ፦ በበጀት ዓመቱ የካሳ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ከቀሪው አረቦን 30% ለመጠባበቂያ ተይዞ ቀሪው ወደ ትርፍ ክፍፍል ይሄዳል።

2) አገልግሎት ሰጪው መሰረታዊ ማህበር ከሆነ፦ በበጀት ዓመቱ የካሳ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ከቀሪው አረቦን 60% ለመጠባበቂያ ተይዞ ቀሪው ወደ ትርፍ ክፍፍል ይሄዳል።

3) ከዚህ መመሪያ በፊት የነበረ ቀሪ አረቦን፦ ቀደም ሲል የነበረ ቀሪ አረቦን ከላይ በዚህ ንዑስ ንዑስ አንቀጽ 1) እና 2) ከተቀመጠው የመጠባበቂያ መጠን በላይ ከሆነ በገቢ ተይዞ ወደ ትርፍ ክፍፍል ይሄዳል።

ሐ) የአረቦን እጥረት ሲያጋጥም፦

1) የተሰበሰበው አረቦን ሙሉ በሙሉ ለካሳ ክፍያ ከዋለ ለመጠባበቂያ የሚይዝ ገንዘብ አይኖርም፤

2) የተከፈለው ካሳ ከተሰበሰበው አረቦን በላይ ከሆነ ማህበራቱ ከሌሎች ገቢዎች ከፍለው በሚቀጥሉት ዓመታት ከሚሰበሰብ አረቦን ያካክሳሉ።

ቅጽ - 1

የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ውል

የ ----------- የቁ/ብ/ህ/ስ/ማ/ር/ ዩኒዬን/ኃላፊነቱ የተወሰነ/

ውል ተቀባይ ስም ------------- ዕድሜ ------------ መለያ ቁጥር -------------- ዞን ------ ወረዳ/ከተማ ----- ቀበሌ ------ ጎጥ -----

መተዳደሪያ ስራ --------- የትዳር ሁኔታ ያገባ ----- ያላገባ ----------- የትዳር አጋር ስም ----

የቤተሰብ ሁኔታ ወንድ ------ ሴት ------- ድምር ------------

የብድር መጠን ---------- የብድር ቆይታ ጊዜ ------ ዓመት ከ----- ቀን----- ወር ---- ዓ.ም እስከ ---- ቀን -----ወር ---ዓ.ም የትዳር አጋር ስም ------------------

የብድርመጠን ---------- የብድር ቆይታ ጊዜ ------ ዓመትከ----- ቀን----- ወር ---- ዓም እስከ ---- ቀን -----ወር ---- ዓ.ም አቶ/ወ/ሮ/ሪ/ት -------ብር ------- ከ ------ እስከ -------- ድረስ ለ --------- ዓመት የሚቆይና ዓመታዊ ---- በመቶ ወለድ የሚከፈልበት ብድር በብድር ውሉ ላይ የተጠቀሱትን ዋሶች ተያዥ አድርጎ ለተበደረው ብድር በራሱ/ሷ እና በትዳር አጋሩ ስም የብድሩን ----- በመቶ አረቦን ከፍሎ ሽፋን የገዛ ሲሆን የ------ የቁ/ብ/ህ/ስ/ማ/ርም በብድር ውል መመለሻ ጊዜው ውስጥ አባሉ/ የትዳር አጋራቸው ለሚያጋጥማቸው የሞት አደጋ አስፈላጊ ማስረጃዎች ተሟልተው እንደቀረቡ በህብረት ስራ ማህበሩ በወራሽነት ለተሰየሙ /በህግ ወራሽነታቸው ለተረጋገጠላቸው የቤተሰብ አባል በሞት ወቅት ያልተከፈለውን ቀሪ ዕዳ፣ ወለድና የቀብር ማስፈጸሚያ ብር 2000.00 (ሁለት ሺ ብር) ለመክፈል ተስማምተናል፡፡

ውል ሰጪ

ስም ----------------

ኃላፊነት -------------

ፊርማ --------- ቀን -------------- -

እማኞች

1.ስም -------- ፊርማ ------- ቀን ------

2.ስም ------- ፊርማ ------ ቀን -----

3.ስም -------- ፊርማ ------ ቀን ------

ቅጽ - 2

የውክልናና ኮሚሽን ክፍያ ውል

ውል ሰጪ

የ ----------- የህብረት ስራ ማህበራት የቁጠባ ብድር ዩኒየን /ኃላፊነቱ የተወሰነ/

አድራሻ ዞን --------- ወረዳ ----- ቀበሌ ስልክ ቁጥር ------- ፖስታ ሳጥን ቁጥር ------

በዚህ ውል መሰረት ውል ተቀባይ እየተባለ ለሚጠራው እና የዩኒየኑ አባል ለሆነው የ -------- መሰረታዊ የቁ/ብ/ህ/ስ/ማ/ር የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት አረቦን ከአባላት ሰብስቦ ገቢ እንዲያደርግልኝና የካሳ ክፍያ እንዲፈጽምልኝ ለአገልግሎቱ ከሚሰበሰበው ጥቅል አረቦን --------- ---------- በመቶ በኮሚሽን መልክ ለመክፈል ተስማምቸ ወክየዋለሁ፡፡

ቅጽ - 3

ውል ተቀባይ

የ----------- መሰረታዊ የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር /ኃላፊነቱየተወሰነ/

አድራሻ ዞን ------ ወረዳ ----- ቀበሌ ----- ስልክ ቁጥር --------

ከላይ ውል ሰጪ በመባል የተጠቀሰው የ------ የህብረት ስራ ማህበራት የቁጠባና ብድር ዩኒየን በወሰነው ኮሚሽን ተስማምቸ የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች አረቦን ሰብስቤ ገቢ ለማድረግ፣ የካሳ ክፍያ ለመፈጸምና አስፈላጊ መረጃዎችና ሪፖርቶችን በመመሪያው ላይ በተቀመጠው አግባብ ለመስጠት ተስማምቼ ውል የፈረምኩ ሲሆን ተግባሬን በታማኝነት እወጣለሁ።

ውልሰጪ	ውልተቀባይ	ዕማኞች
ስም ----------------	ስም ----------	1. ስም -------- ፊርማ ------- ቀን -----
ኃላፊነት -------------	ኃላፊነት --------------	2.ስም ------- ፊርማ ------ ቀን -----
ፊርማ --------- ቀን -------	ፊርማ --------- ቀን -----	-3.ስም -------- ፊርማ ------ ቀን -----

ቅፅ --- 4

የወራሾች የካሳ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ

ለ ------------- የኅብረት ሥራ ማኅበር/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የቁጠባና ብድር ዩኒዩን -------------

ጉዳዩ፡- አቶ/ወሮ--------- በሞት መለየታቸውን ስለማሳወቅ፣

የ----------------- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር አባል የነበሩት አቶ/ወ/ሮ /ሪ/ት -- ------------------- በ ------------------- ምክንያት በቀን ---------------------- ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን ከወሰዱት ብድር ብር ------------------- ውስጥ ቀሪ ብድር ከዋና ብር ------------- ----------------- ከወለድ ብር------------------------ በድምሩ ብር------------ ያለባቸው መሆኑን በፊርማችን እያረጋገጥን በኅብረት ሥራ ማኅበሩ አሰራር እና መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሰረት የብድር የህይወት መድህን ሽፋን ስላላቸው ብድራቸው በብድር የህይወት መድህን እንዲሸፈንና ወራሾቻቸው በዕዳ ተጠያቂ እንዳንሆን እንጠይቃለን።

የአመልካች ስም --------------------------------

ፊርማ ----------------- ቀን -----------------------------------

ቅፅ --- 5

<u>የሞት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት /ማስረጃ</u>

ለ -------------- የኅብረት ሥራ ማኅበር/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የቁጠባና ብድር ዩኒዬን

ጉዳዩ፡- <u>የሞት ማረጋገጫ ማስረጃ ስለመስጠት</u>

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ----------------------------- የተባሉት የ -------- ወረዳ ------- ከተማ ------ ቀበሌ ------ ጎጥ ነዋሪ በ -- ምክንያት በቀን ---------- ወር -------- በ-----------------ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆናቸውን እናረጋግጣለን፡፡

ስም -----------------------------------

ኃላፊነት-------------------------------

ፊርማ --------------------------------

ቀን -------------------------------- ህጋዊ ማህተም ይኖረዋል።

ቅጽ - 6

<u>የብድር የህይወት መድህን አገልግሎት ውል (ለወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ብቻ)</u>

የ ----------- የቁ/ብ/ህ/ስ/ማ/ር/ ዩኒዬን/ኃላፊነቱ የተወሰነ/

ውል ተቀባይ ስም ------------- ዕድሜ ----------- መለያ ቁጥር -------------- ዞን ------ ወረዳ/ከተማ ----- ቀበሌ ------ ጎጥ -----

መተዳደሪያ ስራ --------- የትዳር ሁኔታ ያገባ ----- ያላገባ ----------- የትዳር አጋር ስም ----

የቤተሰብ ሁኔታ ወንድ ------ ሴት ------- ድምር ------------

የብድር መጠን ---------- የብድር ቆይታ ጊዜ ------ ዓመት ከ----- ቀን----- ወር ---- ዓ.ም እስከ ---- ቀን -----ወር ---ዓ.ም የትዳር አጋር ስም -----------------

የብድርመጠን ---------- የብድር ቆይታ ጊዜ ------ ዓመትከ----- ቀን----- ወር ---- ዓም እስከ ---- ቀን -----ወር ---- ዓ.ም አቶ/ወ/ሮ/ሪ/ት -------ብር ------- ከ ------ እስከ -------- ድረስ ለ ------ --- ዓመት የሚቆይ ብድር በብድር ውሉ ላይ የተጠቀሱትን ዋሶች ተያዥ አድርጎ ለተበደረው ብድር በራሱ/ሷ እና በትዳር አጋሩ ስም የብድሩን ----- በመቶ አረቦን ክፍሎ ሽፋን የገዛ ሲሆን የ------ የቁ/ብ/ህ/ስ/ማ/ርም በብድር ውል መመለሻ ጊዜው ውስጥ አባሉ/ የትዳር አጋራቸው ለሚያጋጥማቸው የሞት አደጋ አስፈላጊ ማስረጃዎች ተሟልተው እንደቀረቡ በህብረት ስራ ማህበሩ በወራሽነት ለተሰየሙ /በህግ ወራሽነታቸው ለተረጋገጠላቸው የቤተሰብ አባል በሞት ወቅት ያልተከፈለውን ቀሪ ዕዳና የቀብር ማስፈጸሚያ ብር 2000.00 (ሁለት ሺ. ብር) ለመክፈል ተስማምተናል፡፡

ውል ሰጪ	እማኞች
ስም ----------------	1.ስም -------- ፊርማ ------- ቀን ------
ኃላፊነት -------------	2.ስም ------- ፊርማ ------ ቀን -----
ፊርማ --------- ቀን -------------- -	3.ስም -------- ፊርማ ------ ቀን ------

ቅጽ- 7

የወራሾች የካሳ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ (ለወለድ አልባ የፋይናንስ አገለግሎት ብቻ)

ለ -------------- የኅብረት ሥራ ማኅበር/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የቁጠባና ብድር ዩኒዬን --------------

ጉዳዩ፡- አቶ/ወሮ--------- በሞት መለየታቸውን ስለማሳወቅ፣

የ----------------- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር አባል የነበሩት አቶ/ወ/ሮ /ሪ/ት -- ------------------- በ ------------------- ምክንያት በቀን ---------------------- ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን ከወሰዱት ብድር ብር ------------------ ውስጥ ቀሪ ብድር ብር ------------ ያለባቸው መሆኑን በፊርማችን እያረጋገጥን በኅብረት ሥራ ማኅበሩ አሰራር እና መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሰረት የብድር የህይወት መድህን ሽፋን ስላላቸው ብድራቸው በብድር የህይወት መድህን እንዲሸፈንና ወራሾቻቸው በዕዳ ተጠያቂ እንዳንሆን እንጠይቃለን፡፡

የአመልካች ስም --------------------------------

ፊርማ ----------------- ቀን -----------------------------------